የቅድስት ሥላሴ ወገብረ ክርስቶስ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተ ክርስቲያን በሎስ አንጀለስ

The Holy Trinity - Gebre Cristos
Ethiopian Orthodox Tewahedo
Church in Los Angeles

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

**በተለያዩ ድረ ገጾች "በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ የተወሰኑ ካህናት የማኅበረ ቅዱሳን አባላትን ከቤተክርስቲያን ለማስወጣት ስብሰባ አደረጉ" በሚል ርዕስ ለወጣው አሉባልታ የተሰጠ መግለጫ**

የቅድስት ሥላሴ ወገብረ ክርስቶስ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ከተቋቋመችበት ከ1986 ዓ.ም (1993 GC) ጀምሮ ባለፉት 16 አመታት ብዙ ውጣ ውረዶች የገጠሟት ቢሆንም በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በቅዱሳኑ ጸሎት ፣ ጊዜያዊ ችግር በማይበግራቸው ምእመናኗ፣ ቤተ ክርስቲያኑን በሚያስተዳድረዉ ሰበካ ጉባኤ፣ በማህበረ ካህናትና በሰንበት ት/ቤቱ አባላት ጥንካሬ እስከ ዛሬ ድረስ ሳታስታጉል አገልግሎት ስትሰጥ ቆይታለች።

የቤተክርስቲያናችን አባላትና አገልጋዮች ባላቸው ጽኑ እምነት መሠረት የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ እምነት ፣ ሥርዓትና ትውፊት ሳይበረዝና ሳይከለስ ተጠብቆ እንዲኖር ከፍተኛ ጥረት በማድረጋቸው ዛሬ በአንዳንዶች ዘንድ *"በሎስ አንጀለስ ያለች ገዳም"* በሚል ቅጽል እንድትጠራ ምክንያት ሆኗል። ዛሬም ነገም ወደፊትም እንደ እግዚአብሔር ቸርነት ለአንዲቷ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት መጠበቅ ያላሰለሰ ጥረት ታደርጋለች።

የቅድስት ሥላሴ ወገብረ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ደከመን ሰለቸን ሳይሉ የሚያገለግሉ አረጋውያንና አረጋውያት እንዲሁም ወጣቶች ያሉባት ቤተ ክርስቲያን ናት። ቤተ ክርስቲያኗን የሚያስተዳድረው ሰበካ ጉባኤና ማህበረ ካህናቱ ቤተ ክርስቲያኗ ለቆመችለት አላማ መሳካት ደከመን ሰለቸን ሳየሉ ሌት ተቀን ይሠራሉ። ወጣቶቹም (የማኅበረ ቅዱሳን አባልትን ጨምሮ) በሰንበት ት/ቤትና በሰበካ ጉባኤ አባል ሆነው ኦርቶዶክሳዊ ላህዩን የጠበቀ መዝሙር በማቅረብ ፣ ወጣቶችንና ህጻናትን ትምህርተ ሃይማኖት በማስተማር ፣ ለደብሯ እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

እንዲህ ባለ መልኩ ካህናቱ፣ ሰበካ ጉባኤው ፣ ምእመናኑና ወጣት የሰንበት ት/ቤቱ አባላት በአንድ ሃሳብ ሆነው ለቤተክርስቲያኗ እድገት በመሥራታቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ የራሳችን ህንጻ ቤተ ክርስቲያን ለመግዛት በቅተናል። ይሁን እንጂ ይህን አንድነትና ፍቅር የማይወዱ አካላት በቤተ ክርስቲያናችንና በሌሎች ጥቂት የማይባሉ አብያተ ክርስቲያናት ላይ ሰሞኑን ያሰራጩት አሉባልታ እጅጉን አሳዝኖናል። የቀረበው ክስም በአባቶቻችንና የቤተ ክርስቲያናችን አባላት በሆኑ የማኅበረ ቅዱሳን አባላት መካከል ባለው ፍቅር ፣ አንድነትና መተማመን ላይ አንዳች ነገር ሊያመጣ የማይችል ተራ ወሬ ከመሆን ያለፈ ስፍራ እንደማይሰጠው እናምናለን።

**ቤተ ክርስቲያኗን የሚመራው ሰበካ ጉባኤና ማህበረ ካህናቱ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ በሰ/ት/ቤትና በተለያዩ ኮሚቴዎች ውስጥ የሚያገለግሉ *"የማኅበረ ቅዱሳን አባላትን ከቤተ ክርስትያን ለማስወጣት"* ተደረገ ስለተባለው ስብሰባ ምንም የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በእንዲህ ባለ ኢ-ክርስትያናዊ ተግባር ያልተሳተፉ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ልናረጋግጥ እንወዳለን::**

በአጠቃላይ የቅድስት ሥላሴ ወገብረ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን በአንድ ሲኖዶስ የምትመራና የምታምን ከዚያ የሚወጣውን መመሪያና ትእዛዝ የምትፈጽም ስትሆን ፤ ያዘኑ የሚጽናኑባት ፣ የተሰደዱ የተጠጉባት ወደፊትም የሚጠጉባት ምስካየ ህዙናን ናት እንጂ ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ወይም በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያለውን የማኅበረ ቅዱሳን አባላትን ከቤተ ክርስቲያን ለማራቅ ወይም ለማጥፋት በሚደረግ እኩይ ተግባር ላይ በምንም መልኩ የማትሳተፍ መሆኗን ሁሉም እንዲያውቅ እንፈልጋለን::

ሰላመ እግዚአብሔር አይለየን

ገብረ እግዚአብሔር
ቆሞስ
Komos
**የደብሩ አስተዳዳሪ**